9ኛ አመት ቁጥር 43
9th Year No 43

ባህር ዳር ሚያዝያ 3 ቀን 1997 ዓ.ም
Bahir Dar April 11, 2005

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

ዝክረ-ሕግ

ZIKRE HIG

OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ ብር Price	በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ	ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE	የፖ.ሣ.ቁ 312 P.o. Box

ማውጫ	CONTENTS
ደንብ ቁጥር 27/1997 ዓ.ም.	Regulation No. 27/2005
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሚሊሻ አባላትና አስተባባሪዎች መተዳደሪያ ክልል መስተዳደር ምክር ቤት ደንብ	The Amhara National Regional State Militia Members and Coordinators Administration, Council of Regional Government Regulation

ደንብ ቁጥር 27/1997 ዓ.ም.

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሚሊሻ አባላትና አስተባባሪዎችን ለማስተዳደር የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ

REGULATION No. 27/2005

A COUNCIL OF REGIONAL GOVERNMENT REGULATION ISSUED TO PROVIDE FOR THE ADMINISTRATION OF THE MILITIA MEMBERS AND COORDINATORS IN THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE.

በብሔራዊ ክልሉ ውስጥ በየአደረጃጀት እርከኑ የሚገኙትን የሚሊሻ አባላት አስተዳደራዊ ሁኔታ በዝርዝር የሚያሣይና የሚሊሻ አስተባባሪዎችን ምልመላ፣ ቅጥር፣ ምደባ፣ ዝውውር፣ ስልጠና፣ የደረጃ ዕድገት፣ ስንብት፣ ዲሲፕሊን፣ ጥቅማ ጥቅሞችና የመሣሰሉትን የሚወስን ክልል አቀፍ ስርዓት ቀርጾ በሥራ ላይ ማዋል በማስፈለጉ፤

WHEREAS, it is found necessary to design and implement a regionwide system which ellaborates in spesific terms, the adminstrative matters pertaining to the militia members deployed at each and every organizational hierarchy throughout the National Regional State and which determines the selection, recruitment, assignment, transfer, training, promotion, dismissal, discipline, benefits and the like with respect to coordinators of such militia;

የአማራ ብሔራዊ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 7 እና በክልሉ ሚሊሻ ጽ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 81/1995 ዓ.ም አንቀጽ 2 ፊደል ተራ ቁጥር ሸ ድንጋጌዎች ስር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል::

NOW, THEREFORE, the council of the Amhara National Regional Government, in accordance with the powers vested in it under the provisions of Art. 58 sub-art. 7 of the revised Regional Constitution and art. 2 (h) of the Regional Militia Office establishment proclamation amendement proclamation No.81/2003, hereby issues this regulation as follows:

ክፍል አንድ
ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የሚሊሻ አባላትና አስተባባሪዎች መተዳደሪያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 27/1997 ዓ.ም." ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ:-

1. "የሚሊሻ አስተባባሪ" ማለት በክልሉ ሚሊሻ ጽ/ቤት አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 81/1995 ዓ.ም. አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 3 ፊደል ተራ ቁጥር ሀ ስር የተመለከተው ሲሆን በመለዩ ለባሽ አይነት በጽ/ቤቱ የተቀጠሩትንና በሲቪል ሰርቪስ ህግ የማይሸፈኑትን ድጋፍ ሠጪ

PART ONE
GENERAL PROVISIONS

1. Short Title

This regulation may be cited as ”The Militia Members and Coordinators' Administration Council of Regional Government Regulation No. 27/ 2005.”

2. Definitions

Unless the context otherwise requires, in this regulation:

1. **”Militia Coordinator”** means a person as indicated under Art .2 (a) sub. Art .3 of the Regional Militia Office proclamation amendment proclamation No. 81/2003 and includes those support-providing members who have been recruited by the office as

አባላት ይጨምራል::

2. "የሚሊሻ አባል" ማለት በክልሉ ሚሊሻ ጽ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 13/1988 ዓ.ም. /እንደተሻሻለ/ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተመለከተው ነው::
3. "ቢሮ" ማለት በክልሉ ሚሊሻ ጽ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 81/ 1995 ዓ.ም. አንቀጽ 2 ፊደል ተራ ቁጥር ሀ ንዑስ አንቀጽ 4 ስር የተመለከተው አካል ነው::
4. "ጽህፈት ቤት" ማለት የክልሉ ሚሊሻ ጽ/ቤት ነው::

3. የደንቡ ተፈፃሚነት ወሰን

ይህ ደንብ የክልሉን ሚሊሻ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ እና በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ህግ መሠረት የሚተዳደሩትን ሠራተ→ች ሣይጨምር በማንኛውም የሚሊሻ አስተባባሪና የሚሊሻ አባል ላይ ተፈፃሚ ይሆናል::

military and are not covered by the civil service law.

2. **"Militia Member"** means a person as indicated under Art .2 sub-Art. 1 of the Regional Militia Office establishment proclamation No. 13/1996 as /amended/.
3. **"Bureau"** means the body specified under Art .2(a) sub-Art. 4 of the Militia Office establishment proclamation amendment proclamation No. 81/2003.
4. **"Office"** means the Regional Militia office.

3. Scope of Application of the Regulation

This regulation shall, with the exception of the Head of the Regional Militia Office and those employees administered pursuant to the Regional Civil Service laws, apply to any militia coordinator and members of such militia thereof.

ክፍል ሁለት
ስለሚሊሻ አስተባባሪዎች ምልመላ፣ ሥልጠና፣ ቅጥር፣ ምደባና ዝውውር

PART TWO
SELECTION, TRANINING, RECRUITMENT, ASSIGNMENT AND TRANSFER OF MILITIA COORDINATORS

4. ምልመላ

1. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መመዘኛዎች የሚያሟላና ፍላጎት ያለው ማንኛውም ሰው በሚሊሻ አስተባባሪነት ሊመለመል ይችላል:-

   ሀ. ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ የሆነ፣
   ለ. ለክልሉና ለፌዴራሉ ህገጋተ መንግስታት ታማኝ የሆነ፣

4. Selection

1. Any person wishing to serve as a militia coordinator may, upon the fulfillment of the criteria specified herebelow, be selected as such where he:
   a. Is an Ethiopian citizen;
   b. Loyal to the Regional and Federal Constitutions;

ሐ. በፀጥታ ሥራ ቢያንስ ለሶስት አመታት ያገለገለ፤

መ. መልካም ሥነ-ምግባር ያለው፣

ሠ. ቢያንስ የ10ኛ ክፍል ትምህርቱን ያጠናቀቀ፣

ረ. ዕድሜው ከ21 ዓመት ያላነሰ::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለሚሊሻ አስተባባሪነት የሚደረገው ምልመላ በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን ብሔር-ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ተዋጽኦ ከግምት ውስጥ ያስገባ ይሆናል::

5. ስለሥልጠና

1. ማንኛውም የሚሊሻ አስተባባሪ ስራ ከመጀመሩ በፊት መሠረታዊ የሚሊሻ አስተባባሪነት ሥልጠና ይሰጠዋል:: የስልጠናው አላማም ለሕግ የበላይነት የሚቆምና ብቃት ያለው የሚሊሻ ሀይል አስተባባሪ መፍጠር ነው:: ዝርዝሩ ይህንን ደንብ መሠረት በማድረግ ወደፊት በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል::

2. የሚሊሻ አስተባባሪዎችና አባላቱ የስልጠና ካሪኩለም በጽ/ቤቱ ይዘጋጃል::

6. ስለቅጥር

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 4 እና 5 ድንጋጌዎች መሠረት የተመለመለ እና የሠለጠነ ማንኛውም እጩ የሚሊሻ አስተባባሪ በጽ/ቤቱ የሚዘጋጀውን የቅጥር ውል ይፈርማል:: ቅጥሩ የሚፀናው ስልጠናውን መውሰድ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ሲሆን ይኸውም በቅጥር ውሉ ላይ ይገለፃል:: ዝርዝሩ ወደፊት በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል::

c. Has served at least for 3 years in security duties;

d. Has a good ethical conduct;

e. Has at least completed 10th grade in pursuance of his education;

f. Is not below the age of 21 years.

2. Without prejudice to the provisions of sub-Art. 1 of this article hereof, the selection to be carried out for the position of militia coordination shall take into account the fair representation of nation-nationalities and peoples residing in the Regional state.

5. Training

1. Any militia coordinator shall receive basic training in militia coordination prior to commencing his duties. Thus, the aim of such training is to create an efficient coordinator to be in charge of the militial force and committed for the rule of law. Details shall be determined by a directive to be issued pursuant to this regulation.

2. The training curriculum of the militia coordinators and members there of shall be prepared by the office.

6. Recruitment

1. Any prospective militia coordinator who has been selected and trained pursuant to Arts. 4 and 5 of this regulation hereof shall sign an employment contract prepared by the office. Such recruitment shall be effective as of the date of having commenced the taking of the training, which needs to be specified in the employment contract. Details shall be determined by a directive to be issued in the future.

2. ተመሣሣይ አገልግሎት ይሰጥ ከነበረበት ከሌላ የመንግስት መስሪያ ቤት ተዛውሮ የመጣ ከሆነ የቆየ የአገልግሎት ጊዜው የሚያዝለት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በሚሊሻ አስተባባሪነት የተቀጠረ ማንኛውም ሰው ሰባት አመት የአገልገሎት ግዴታ ይኖርበታል። የሰባት ዓመት የግዴታ አገልግሎት ጊዜው መቆጠር የሚጀምረው ቅጥሩ ከተፈፀመበት ቀን ጀምሮ ይሆናል።

2. Without prejudice to the consideration of his previous service years, if he has moved by transfer from another government office where he had been rendering similar services, any person recruited to be a militia coordinator shall serve for a compulsory period of seven years. Such a period of compulsory service running for seven years shall be calculated as from the date of the recruitment having been made thereof.

7. ስለምደባ

ማንኛውም አዲስ የተቀጠረ የሚሊሻ አስተባባሪ ሥልጠናውን ከጨረሰ በኋላ በክልሉ ውስጥ በየትኛውም ቦታ በጽ/ቤቱ ይመደባል።

7. Assignment

Any newly-recruited militia coordinator shall, upon completion of his training, be assigned by the office anywhere within the Regional State.

8. ስለዝውውርና በተጠባባቂነት ስለመመደብ

1. ጽ/ቤቱ ለሥራው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ማንኛውንም የሚሊሻ አስተባባሪ ከአንድ የሥራ መደብ እኩል ደረጃና ደመወዝ ወዳለው ሌላ ተመሣሣይ የሥራ መደብ ወይም ከአንድ የሥራ ቦታ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ በማዛወር ሊያሠራ ይችላል።

1. The office may, whenever it is found to be necessary for the duty, transfer any militia coordinator from one position to another similar position with an equal grade and salary or from one place of work to another and their by employ accordingly.

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በውስጥ ዝውውር ሊሞላ በሚችል የሥራ መደብ ላይ መሥራት የሚፈልጉ ሌሎች የሚሊሻ አስተባባሪዎች ሲኖሩ ዝውውሩ የሚፈፀመው በውድድር ይሆናል።

2. Any assignment envisaged under sub-Art 1. of this article hereof shall be carried out on the basis of competition where there are other militia coordinators interested to be palced in any postion of work open for occupation by an internal transfer.

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተደነገገው ቢኖርም ጽ/ቤቱ ሥራው እንዳይበደል የአንድን የሚሊሻ አስተባባሪ ደመወዝ ሣይቀንስና ደረጃውን ወይም የያዘውን የሥራ አይነት ሣይጠብቅ ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ በጊዚያዊነት አዛውሮ ማሠራት ይችላል።

3. Notwithstanding the provisions of sub-Art 1. of this article hereof, the office may temporarily assign, for the purpose of the duty, a militia coordinator to a position of work, without affecting his salary, irrespective of his grade and the type of

4. ማንኛውም የሚሊሻ አስተባባሪ በጤና መታወክ ምክንያት በያዘው የሥራ መደብ ላይ ወይም ባለበት የሥራ ቦታ ሊሠራ አለመቻሉ በህኪም ሲረጋገጥ፡-

   ሀ. በተመሣሣይ ደረጃ ሊመደብ የሚችልበት ክፍት የሥራ ቦታ ካለ በያዘው ደረጃ ወይም

   ለ. በተመሣሣይ ደረጃ ሊመደብ የሚችልበት ክፍት የሥራ ቦታ ከሌለና የሚሊሻ አስተባባሪው በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ለመስራት ፈቃደኛ ሆኖ ከተገኘ ደረጃው ተቀንሶ ወደሚስማማው የሥራ መደብ ወይም የሥራ ቦታ ይዛወራል::

5. ሁኔታዎች ሲያስገድዱ ጽ/ቤቱ አንድን የሚሊሻ አስተባባሪ ከፍ ያለ ደረጃ ባለው የሥራ መደብ ላይ በተጠባባቂነት እንዲሠራ ማድረግ ይችላል፣ ሆኖም አስተባባሪውን ከአንድ አመት በላይ በተጠባባቂነት ማሠራት አይቻልም::

ክፍል ሶስት
ስለሚሊሻ አስተባባሪዎች የሥራ ሰዓትና ልዩ ልዩ ፈቃዶች

9. መደበኛ የሥራ ሰዓት

1. በዚህ ደንብ መሠረት የክልሉ ሚሊሻ አስተባባሪ በቀን 24 ሰዓት፣ በሣምንት ሰባት ቀናት፣ በወር 30 ቀናትና በዓመት 365 /6/ ቀናት ያለማቋረጥ አገልግሎት ይሰጣል::

work he is engaged in for the period, not exceeding one year.

4. Where it is medically proven that any militia coordinator is, because of ill-health, unable to keep on working in the postion or place of work he has already occupied thereof, he shall be transferred to another suitable positon or place of work:
   a. with the same grade, as he has been holding if there exists a vacant position of work for possible assignment; or
   b. with a lower grade, where a vacant position of the same grade is not available and he is, therefore, willing to be transferred to a position of lower grade as a consequence.

5. Where circumstances so campell, the office may assign a militia coordinator to a higher position in an acting capacity; provided, however, that no such coordinator may be assigned in such capacity for more than a year.

PART THREE
WORKING HOURS AND VARIOUS LEAVES GOVERNING MILITIA COORDINATORS

9. Normal Working Hours

1. The service of the Regional Militia Coordinator shall, pursuant to this regulation, be uninterruptedly rendered for 24 hours a day, 7 days a week, 30 days a month and 365(6) days a year.

2. የማንኛውም ሚሊሻ አስተባባሪ መደበኛ የሥራ ሰዓት በቀን 8 ሰዓት ሆኖ በሣምንት ከ48 ሰዓት መብለጥ የለበትም። ሆኖም በአስቸኳይ ጉዳይ ወይም በልዩ የፀጥታ ሥራ ምክንያት የትርፍ ሰዓት ሥራ እንዲሠራ በቅርብ አለቃው ከታዘዘ መሥራት ይኖርበታል። ለሠራበት የትርፍ ሰዓት ሥራ የማካካሻ እረፍት ይሠጠዋል።

10. የዓመት ዕረፍት ፈቃድ መርህ

1. የሚሊሻ አስተባባሪ የዓመት ዕረፍት ፈቃድ የሚሰጠው ለተወሰነ ጊዜ በማረፍ አገልግሎቱን በታደሰ መንፈስ እንዲቀጥል ለማስቻል ነው።

2. የዓመት ዕረፍት ፈቃድ በዚህ ደንብ አንቀጽ 11 መሠረት የሚሰላና በገንዘብ የማይለወጥ ይሆናል።

11. የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ስሌት

1. አንድ ዓመት ያገለገለ የሚሊሻ አስተባባሪ 20 የሥራ ቀናት የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ያገኛል፣

2. ከአንድ ዓመት በላይ ያገለገለ የሚሊሻ አስተባባሪ ለእያንዳንዱ ተጨማሪ ዓመት አንድ የሥራ ቀን እየታከለበት የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ያገኛል፣ ሆኖም የሚሰጠው የአንድ ዓመት የዕረፍት ፈቃድ በጠቅላላው ከ30 የስራ ቀናት መብለጥ የለበትም።

12. የዓመት ዕረፍት ፈቃድ አሰጣጥ

1. የዓመት ዕረፍት ፈቃድ በበጀት ዓመቱ ውስጥ በሙሉ ሣይሸራረፍ መሠጠት አለበት፣

2. የሚሰጠው የዓመት ዕረፍት ፈቃድ በተቻለ መጠን የጽ/ቤቱን ተልዕኮ የማያደናቅፍ እና በፀጥታ ተግባራት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የማያሣድር መሆን ይኖርበታል።

2. The normal working hours of any militia coordinator constitute 8 hours a day and may not exceed 48 hours a week; provided, however, that, where he is instructed by his immediate superior to work over time due to emergency or special security works, the coordinator shall be obliged to show up for duty. Nevertheless he shall be given a compensatory leave thereto.

10. Principle of Annual Leave

1. The purpose of granting annual leave to a militia coordinator is to enable him get a break for a limited time and resume his services with a renewed sprit.
2. Annual leave shall be calculated pursuant to article 11 of this regulation and there shall be no payment in lieu of it.

11. Calculation of Annual Leave

1. A militia coordinator shall be entitled to annual leave of 20 working days for his first year of service;
2. A militia coordinator, having the service of more than one years, shall be entitled to an additional leave of one working day for every additional year of service; provided, however, that the maximum duration of the said annual leave may not exceed 30 working days.

12. Granting of Annual Leave

1. Annual leave shall be granted fully without interruption within the current fiscal year.
2. The annual leave to be granted may not, as much as possible, obstruct the mission of the office and adversely affect the security duties.

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተደነገገው ቢኖርም አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ የዓመት ዕረፍት ፈቃዱ ተከፋፍሎ ሊሰጥ ይችላል::

4. ማንኛውም በአመት ዕረፍት ፈቃድ ላይ ያለ የሚሊሻ አስተባባሪ አስገዳጅ ሁኔታ ሲፈጠር የዕረፍት ጊዜውን አቋርጦ እንዲገባ ሊደረግ ይችላል:: ሆኖም ያልተጠቀመበት ጊዜ ለቀጣዩ እረፍት ይታሰብለታል::

3. Notwithstanding the provisions of sub-Art .1 of this article hereof, annual leave may be granted in an interrupted manner, as deemed necessary.

4. Where compelling circumstances are so created, any militia coordinator who is on annual leave may be made to interrupt his leave and resume work; provided, however, that the unuitilized leave shall be calculated in his favour during the next break.

13. የዓመት ዕረፍት ፈቃድን ስለማስተላለፍ

1. የዓመት ዕረፍት ፈቃድ በበቂ ምክንያት በበጀት ዓመቱ ውስጥ ጥቅም ላይ ያልዋለ ሲሆን ወደ ሚቀጥለው የበጀት ዓመት ሊተላለፍ ይችላል::
2. ከሁለት የበጀት አመታት በላይ አንድን የአመት ዕረፍት ፈቃድ ወደሚቀጥለው የበጀት አመት ማስተላለፍ አይቻልም::

13. Postponement of Annual Leave

1. Where an annual leave has not been utilized during the current fiscal year for a sufficient cause, it may be postponed to the next fiscal year.
2. It may not be possible to postpone an annual leave for more than two fiscal years.

14. የህመም ፈቃድ

1. ማንኛውም የሚሊሻ አስተባባሪ በሕመም ምክንያት ሥራ መስራት ያልቻለ እንደሆነ በሚያቀርበው የህክምና ማስረጃ መሠረት የህመም ፈቃድ ይሰጠዋል::
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ለሚሊሻ አስተባባሪ የሚሰጥ የህመም ፈቃድ በተከታታይ ወይም በተለያየ ጊዜ ቢወሰድም በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ የተሰጠው የህመም ፈቃድ ስምንት ወር የደረሰ እንደሆነ ወይም በአራት አመት ውስጥ የተሰጠው የህመም ፈቃድ አስራ ሁለት ወር የደረሰ እንደሆነ ሌላ የህመም ፈቃድ አይሰጠውም::
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የሚሰጥ የህመም ፈቃድ ለመጀመሪያዎቹ ሶስት ወራት ከሙሉ ደመወዝ ጋር ለተከታዩቹ ሶስት ወራት ከግማሽ ደመወዝ እና ለመጨረሻዎቹ

14. Sick-Leave

1. Any militia coordinator shall be entitled to sick leave as per the certificate he produces where he is unable to work due to sickness.
2. Where the duration of sick leave to be granted to the militia coordinator in accordance with sub-Art .1 of this article hereof has reached eight months in one year or twelve months in four years, whether taken consecutively or intermittently, he may not be entitled to another leave.
3. The sick-leave to be granted in accordance with sub-Art .2 of this article hereof shall be with full pay for the first three months, with half pay for the following three

ሁለት ወራት ያለደመወዝ ይሆናል፣

4. ማንኛውም የሚሊሻ አስተባባሪ በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ የህክምና ማስረጃ ሣያቀርብ የተጠቀመበት የህመም ፈቃድ ከ6 ቀናት በላይ ሆኖ ሲገኝ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ካለው የአመት ዕረፍት ጊዜ ይቀነስበታል::

15. የሀዘን ፈቃድ

1. ማንኛውም የሚሊሻ አስተባባሪ የትዳር ጓደኛ፣ ልጅ፣ ወላጅ፣ እህት ወይም ወንድም የሞተበት እንደሆነ ደመወዝ የሚከፈልበት የ3 ቀናት የሀዘን ፈቃድ ይሰጠዋል::

2. የሚሊሻ አስተባባሪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር ከተመለከቱት ውጪ ሌላ የቅርብ ዘመድ ወይም ወዳጅ የሞተበት እንደሆነ ደመወዝ የሚከፈልበት የአንድ ቀን የሃዘን ፈቃድ ይሰጠዋል፣ ሆኖም በዚህ አይነት በአንድ የበጀት አመት ውስጥ የሚሰጠው የሀዘን ፈቃድ ከ6 ቀን መብለጥ አይኖርበትም::

16. ልዩ ፈቃድ

ማንኛውም የሚሊሻ አስተባባሪ በሚከተሉት ሁኔታዎች ልዩ ፈቃድ ይሰጠዋል:-

1. ጋብቻ ሲፈጽም ለሶስት የሥራ ቀናት፣

2. ከፍርድ ቤት ወይም ከሌሎች ስልጣን ከተሠጣቸው አካላት መጥሪያ ሲደርሰው የተጠራበት ጉዳይ እስከሚያበቃበት ጊዜ ድረስ፤

3. በህዝብ ምርጫ ሥልጣን የሚይዙ የመንግሥት ባለሥልጣናትን ለመምረጥ አስፈላጊ ሲሆን ምርጫው ለሚወስድበት ጊዜ፤

4. በጽ/ቤቱ ዕቅድ በተገኘ የትምህርት ወይም የስልጠና ዕድል በሀገር ውስጥ ወይም በውጪ ሀገር እንዲማር ሲወሰን ትምህርቱ ወይም

months and without pay for the last two months.

4. Where the sick-leave used by any militia coordinator without producing medical certificates is found to have exceeded six days, it shall be deducted from his annual leave in the current fiscal year.

15. Mourning Leave

1. Any militia coordinator shall be entitled to mourning leave with pay for three consecutive days in the event of the death of his spouse, child, parents, sisiter or brother

2. The militia coordinator shall be entitled to leave with pay for one day in the event of the death of his close relative or friend other than those specified under sub. Art (1) of this article hereof; provided; however, that such a leave may not exceed six days within one fiscal year.

16. Special Leave

Any militia coordinator shall be entitled to special leave on the following conditions:

1. Three working days, when concluding marriage;
2. For as long as the time required to accomplish the purpose, for which he has been called upon, when summoned to appear befor a court or other competent bodies;
3. For the period which the voting process may take, where he has to participate in an election of public officials;
4. For the time taken to complete the education or training awarded to him, where he has to participate in such

ስልጠናው እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ፤

5. ለጽ/ቤቱ አሣውቆ በሚከታተለው ትምህርት አማካኝነት ለሚወስደው ፈተና በሚያስፈልጉት ቀናት ልክ::

17. ያለደመወዝ ስለሚሰጥ ፈቃድ

ማንኛውም የሚሊሻ አስተባባሪ በቂ ምክንያት ሲያቀርብና የጽ/ቤቱን ተልዕኮ የማይጎዳ ሲሆን በጽ/ቤቱ ኃላፊ ፈቃድ በአምስት ዓመት ውስጥ ለአንድ ጊዜ ብቻ ለ30 ተከታታይ የሥራ ቀናት ያለደመወዝ የሚሰጥ ልዩ ፈቃድ መውሰድ ይችላል::

18. የፈቃድ አጠያየቅ ሁኔታ

ማንኛውም የሚሊሻ አስተባባሪ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ካልገጠመው በስተቀር ፈቃድ የሚጠይቀው በጽሁፍ መሆን ይኖርበታል::

ክፍል አራት
ስለሚሊሻ አስተባባሪዎች ደመወዝ፣ የደረጃ ዕድገት፣ ህክምናና ካሣ

ንዑስ ክፍል አንድ
ስለደመወዝና የደረጃ ዕድገት

19. ደመወዝና አበል

1. ማንኛውም የሚሊሻ አስተባባሪ በክልሉ መንግስት በሚወሰነው መሠረት:-

   ሀ. ለተመደበበት የሥራ መደብ የተመለከተው ደመወዝ ይከፈለዋል

opportunities obtained in accordance with the plan of the office;

5. For the days necessary for him to take the examination in pursuance of his education he has been attending with the knowledge of the office.

17. Leave without pay

Any militia coordinator may be entitled to special leave without pay by the permission of the office head for 30 consecutive working days once in a period of five years provided that he has requested for same along with sufficient grounds and such an action does not jeopardize the mission of the office.

18. Application for Leave

Unless prevented from so doing by force majeaure, any militia coordinator shall have to request for his annual leave in writing.

PART FOUR
SALARY, RANK PROMOTION, MEDICATION AND COMPENSATION OF MILITIA COORDINATORS
SUB-PART ONE
SALARY AND RANK PROMOTION

19. Salary and Allowances

1. Any militia coordinator shall, pursuant to the decisions of the Regional Government, be:
   a. Entitled to a payment of the salary specified to the job title he has been assigned to;

ለ. የቀለብ የመንገዣ አበልና እንደአስፈላጊነቱ የሚወሰን ሌላ አበል ሊከፈለው ይችላል::

2. የሥራ አፈፃፀም ውጤቱ አጥጋቢ የሆነ ማንኛውም የሚሊሻ አስተባባሪ በያዘው ደረጃ በየሁለት ዓመቱ የእርከን ጭማሪ ያገኛል::

20. ደመወዝ ስለሚያዝበት ወይም ስለሚቆረጥበት ሁኔታ

1. የማንኛውም የሚሊሻ አስተባባሪ ደመወዝ፡-

ሀ. በራሱ ስምምነት

ለ. በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም

ሐ.በህግ በተደነገገው መሠረት ካልሆነ በስተቀር ሊያዝ ወይም ሊቆረጥ አይችልም::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ለ እና ሐ መሠረት ከሚሊሻ አስተባባሪው ደመወዝ የሚቆረጥ ማናቸውም ቅናሽ ከአንድ ሶስተኛው መብለጥ የለበትም::

21. ስለደረጃ ዕድገት

1. ማንኛውም የሚሊሻ አስተባባሪ የደረጃ ዕድገት የሚያገኘው በውድድር ይሆናል::

2. ጽ/ቤቱ የደረጃ ዕድገት የሚሰጥበትን ዝርዝር መመሪያ በማውጣት በቢሮው አስፀድቆ በሥራ ላይ ያውላል::

b. Possibely paid food, transport and other allowances to be determined, as may be deemed necessary.

2. Any militia coordinator who has satisfactory performance evaluation result shall be entitiled to salary scale increament every two years by the position he holds.

20. Withholding or Deduction of Salary

1. The salary of any militia coordinator may not be withheld or deducted except in accordance with:
   a. the consent of himself;
   b. a court order; or
   c. the provisions of the law.

2. Any amount of monthly deductions from the salary of a militia coordinator to be made pursuant to sub-Art. (1) ”b” and ”c” of this article hereof may not exceed one-third of his salary.

21. Rank Promotion

1. Any militia coordinator shall obtain rank promotion on the basis of competition.

2. The office shall issue a detailed directive designed to facilitate the rank promotion and implement same up on approval by the Bureau.

ንዑስ ክፍል ሁለት
ስለህክምናና ካሣ

22. የህክምና አገልግሎት

1. ማንኛውም የሚሊሻ አስተባባሪ፡-

ሀ. ከፀጥታ ስራ ጋር በቀጥታ ተዛማጅነት ባለው ተልዕኮ ላይ ተሠማርቶ እያለ ቢቆስል በጽ/ቤቱ ወጪ በሃገር ውስጥ በሚገኙ የመንግስት ተቋማት የህክምና አገልግሎት ይሰጠዋል::

ለ. በሥራ ላይም ሆነ ከሥራ ውጪ ሲታመም በክልሉ መንግስት ወጪ በነፃ የመታከም መብት አለው::

ሐ.የትዳር ጓደኛውንና 18 አመት ያልሞላቸውን ልጆቹን በመንግስት የጤና ተቋማት በነፃ የማሣከም መብት አለው::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ቁጥሮች ለ እና ሐ ስር የሰፈሩት መብቶች ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችለው ዝርዝር የወጪ መጋራት ማስፈፀሚያ መመሪያ ይህንን ደንብ መሠረት በማድረግ ወደፊት ተጠንቶ በቢሮው የሚወጣ ይሆናል::

23. ስለጉዳት ካሣ

ማንኛውም የሚሊሻ አስተባባሪ፡-

1. በሥራ ላይ በደረሰበት ጉዳት ምክንያት አካላዊ ችሎታ ማጣቱ በህኪም ሲረጋገጥና ጭራሹን ሥራ መቀጠል የማይችል ሲሆን ተመጣጣኝ የጉዳት ካሣ ይከፈለዋል:: የካሣው መጠን

SUB-PART TWO
MEDICAL CARE AND COMPENSATION

22. Medical Service

1. Any militia coordinator shall:
   a. be entitiled to a medical service from the governement medical institutions within the country with the expense being covered by the office, provided that he is wounded while he is engaged in a mission directly related to security works;
   b. have the right to obtain medical services free of charge whenever he falls sick while on duty or out of duty with the expense being covered by the Regional Government;
   c. Have the right to obtain the provision of medical services free of charge from government medical institutions for his spouse and children below 18 years of age.
2. The detailed expenditure-sharing implementation directive which enables one to use the rights specified under sub-Art (1) B and C of this article hereof shall, on the basis of this regulation, be studied and issued by the Bureau in the future.

23. Compensation For injuries

Any militia coordinator shall:

1. be entitled to an equivalent payment of compensation for injuries where it is certified by a physician that he has lost his physical ability and full working potential

በቢሮው ተጠንቶ በክልሉ መስተዳድር ም/ቤት በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል። መደበኛ ጡረታውም አግባብ ባለው ህግ መሠረት ይከበርለታል።

2. የደረሰበት ጉዳት ከፊል ሆኖ ወደቀድሞ ተግባሩ መመለስ ያልቻለ እንደሆነ ወደሚመጥነው የሥራ መደብ ተዛውሮ እንዲሠራ ይደረጋል።

3. በሥራ ላይ በደረሰበት ጉዳት ምክንያት የተሰዋ ሲሆን አግባብ ባለው ህግ መሠረት የወራሾቹ መብት የተጠበቀ ይሆናል።

4. ጉዳቱ የደረሰበት በሶስተኛ ወገን ጥፋት ሲሆን ጽ/ቤቱ ከአጥፊው ወገን ላይ ለተጐጅው የከፈለውን የጉዳት ካሣ የመጠየቅ መብት ይኖረዋል። እንዲህም ሲሆን የሚሊሻ አስተባባሪው ከአጥፊው 3ኛ ወገን ላይ የጉዳት ካሣውን በቅድሚያ ተቀብሎ ከሆነ ጽ/ቤቱ በዚህ ደንብ መሠረት ለተጎጅው መክፈል የነበረበትን የገንዘብ መጠን ማስቀረት ይችላል።

due to an employment injury. The amount of such a compensatory pay shall be determined in a directive to be issued by the Bureau upon approval by the Council of the Regional Government. His normal pension shall as well be secured in accordance with the relevant laws.

2. Be moved though transfer into a job title considered manageable for him where he is unable to resume his original duties because of partial disability occurring to him.

3. The rights of his heirs shall be respected pursuant to the relevant laws, where he is sacrificed due to an employment injury

4. where the injury is caused to a militia coordinator due to the fault of a third party, the office may claim for the payment it has already made in favor of the injured person; provided, however, that, where the militia coordinator had already received himself the compensatory pay from such a party having brought about the harm, the office may, pursuant to this regulation, withhold the amount of money it could possibly have released to the person injured.

ክፍል አምስት
አገልግሎት ስለማቋረጥና ስለማራዘም

24. በራስ ፈቃድ ከሥራ ስለመሰናበት

1. ማንኛውም የሚሊሻ አስተባባሪ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የግዴታ ጊዜውን ካጠናቀቀ የሶስት ወር የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በጽሁፍ በመስጠት ሥራውን በገዛ ፈቃዱ ለመልቀቅ ማመልከት ይችላል::
2. መልቀቂያ ጠያቂው የሚሊሻ አስተባባሪ ለሥራው እጅግ አስፈላጊና በቀላሉ ለመተካት የማይቻል ሆኖ ሲገኝ የጽ/ቤት ኃላፊው የመልቀቂያ ጥያቄውን ከ6 ወር ለማይበልጥ ጊዜ ማራዘም ይችላል::
3. መልቀቂያ ጠያቂው የግዴታ አገልግሎት ዘመኑን ሣያጠናቅቅ ወይም ልዩ ሥልጠና ወስዶ የሚፈለግበትን አገልግሎት ሣያበረክት ለመልቀቅ ያመለከተ እንደሆነ ለሥልጠና የወጣውን ማናቸውንም ወጪ ለጽ/ቤቱ መተካት ይኖርበታል:: ዝርዝሩ ወደፊት በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል::

25. በሕመም ምክንያት ለአገልግሎት ብቁ ስላለመሆን

ማንኛውም የሚሊሻ አስተባባሪ በዚህ ደንብ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 2 በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ወደ ሥራ ካለተመለሰ ወይም በአንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ጉዳት ደርሶበት ሙሉ በሙሉ ስራውን ለመቀጠል ብቁ አለመሆኑ ሲረጋገጥ አገልገሎቱ እንዲቋረጥ ይደረጋል::

PART FIVE
TERMINATION AND EXTENSION OF SERVICE

24. Resignation

1. Any militia coordinator may, upon completion of his obligatory service pursuant to art 6, sub. Art 2 of this regulation hereof, apply to resign giving a three-months prior notice in writing.
2. Where the service of the militia coordinator is indispensable and it is thus impossible to replace him easily, the managing head of the office may delay the release sought for a period not exceeding six months.
3. A militia coordinator who has applied for resignation prior to completing the period of his obligatory service or has received special training, but virtually rendered no service required of him, shall re-imburse to the office the corresponding expenses incurred due to the training provided thereto. Detailes shall be determined by a directive to be issued in the future.

25. Inability to Render Service due to Illness

The service of any militia coordinator shall be terminated where he is unable to resume work within the period specified under Art 14 sub Art. 2 or where he, in accordance with Art .23 sub Art .1 of this regulation hereof, is medically declared to be permanently incapable of carrying on his duties.

26. በችሎታ ማነስ ምክንያት ከሥራ ስለመሰናበት

1. ማንኛውም የሚሊሻ አስተባባሪ የሥራ አፈፃፀም ውጤቱ በተከታታይ ለሁለት ጊዜ ከአጥጋቢ በታች ከሆነ ከሥራ ሊሰናበት ይችላል።

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቢኖርም ለተከታታይ አምስት አመታት ከፍተኛ የሥራ አፈፃፀም ውጤት ሲያገኝ የነበረ የሚሊሻ አስተባባሪ ለሶስት ተከታታይ ጊዜያት ከአጥጋቢ ነጥቦች በታች ካላስመዘገበ በስተቀር ከሥራ አይሰናበትም።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ወይም 2 ድንጋጌዎች መሠረት አንድን የሚሊሻ አስተባባሪ ከሥራ ማሰናበት የሚቻለው፦
   ሀ. ለያዘው የሥራ መደብ የሚያስፈልገው ስልጠና ተሰጥቶት በጠቅላላው ሣይሻሻል ሲቀር ወይም
   ለ. በንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ተመሣሣይ ወደ ሆነ ወይም ሊሰራው ወደ ሚችለው ሌላ የሥራ መደብ ተዛውሮ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ መሻሻል ሣያሣይ ሲቀር ወይም
   ሐ. በንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የአንድ አመት ተኩል ጊዜ ተሰጥቶት ራሱን ለማሻሻል ያልቻለ እንደሆነ ብቻ ይሆናል።

26. Termination of service on Grounds of Inefficiency

1. The service of any militia coordinator may be terminated where his performance evaluation result has been found to be under satisfactory for two consecutive evaluation periods.
2. Notwithstanding the provision of sub art 1 of this article hereof, a militia coordinator, whose performance evaluation result has been found to be outstanding for the preceeding five consecutive years, may not be dismissed on grounds of inefficiency unless his performace result becomes unsatisfactory for the following three consecutive evaluation periods.
3. The termination of service under sub Arts 1 or 2 of this article shall be effected where:
   a. he has totally failed to show improvement after he has been given the training required for his position; or
   b. hasn't shown improvements within one year after he has been transferred to another similar position he is capable of performing; or
   c. he is not capable of improving himself after having been given a period of one and half years pursuant to sub-Art .2 of this article hereof.

27. በዲስፕሊን ምክንያት ከሥራ ስለመሰናበት

ማንኛውም የሚሊሻ አስተባባሪ በዚህ ደንብ አንቀጽ 33 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ቁጥር ሠ ድንጋጌ መሠረት ከሥራ እንዲሰናበት የዲሲፕሊን ቅጣት የተወሰነበት እንደሆነ አገልግሎቱ እንዲቋረጥ ይደረጋል። ሆኖም የተላለፈበት የዲሲፕሊን ውሣኔ በይግባኝ ከተሰረዘለት ወይም ከተሻሻለለት በክርክር ወቅት ሣይከፈለው የቀረው ደመወዝ ታስቦ ያለወለድ ይከፈለዋል።

27. Termination of service on Disciplinary Grounds

The service of any militia coordinator shall be terminated where a disciplinary penalty is imposed on him pursuant to the provision of Art 33 sub-Art.1 E of this regulation hereof; provided, however, that, when such a displinary penalty has been cancelled or varied on an appeal, the militia coordinator shall be entitled to the payment of his salary withheld during the period of appeal without interest.

28. በዕድሜ ምክንያት አገልግሎት ስለማቋረጥ

1. **ማንኛውም የሚሊሻ አስተባባሪ አገልግሎቱ ካልተራዘመ በስተቀር በሕግ ከተወሰነው የመጦሪያ ዕድሜ ከደረሰበት የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ያለተጨማሪ ሥነ-ሥርዓት አገልግሎቱ እንዲቋረጥ ይደረጋል፣**
2. **የሚሊሻ አስተባባሪው ጡረታ ከመውጣቱ ከሶስት ወራት በፊት በጽሁፍ እንዲያውቀው መደረግ አለበት፣**
3. **በማናቸውም ምክንያት አገልግሎት ያቋረጠ የሚሊሻ አስተባባሪ የሥራውን አይነት፣ የአገልግሎት ዘመኑን፣ ሲከፈለው የነበረውን ደመወዝ ልክና ከሥራ የተሰናበተበትን ምክንያት የሚገልፅ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል።**

28. Retirement

1. Unless it is so extended, the service of any militia coordinator shall be terminated without additional procedure as of the last day on which he has attained the retirement age as determined by law.
2. The militia coordinator shall be notified in writting of his retirement three months in advance.
3. Where a militia coordinator has terminated his service for any reason, he shall be provided with a certificate of service indicating the type of work he was engaged in, duration of his service, the amount of his current pay and the reasons for termination thereof.

29. አገልግሎት ስለማራዘም

1. **ማንኛውም የሚሊሻ አስተባባሪ የመጦሪያ ዕድሜው ከደረሰ በኋላ በአንድ ጊዜ እስከ 5 ዓመት በጠቅላላው ደግሞ ከአሥር አመት ለማይበልጥ ጊዜ አገልግሎቱን ማራዘም ይቻላል።**

29. Extension of Service

1. The duration service of any militia coordinator may be extended beyond his retirment age for a period up to five years at a time and for a period not exceeding ten years in total.

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የአንድን የሚሊሻ አስተባባሪ አገልግሎት ማራዘም የሚቻለው፡-
   ሀ. የሚሊሻ አስተባባሪው ትምህርት፣ ልዩ ዕውቀት፣ ችሎታና ልምድ ለጽ/ቤቱ ሥራ እጅግ ጠቃሚ ሆኖ ሲገኝ፤
   ለ. የእርሱ ተተኪ የሚሆን ሰራተኛ በቀላሉ ለማግኘት አለመቻሉ ሲረጋገጥ፤
   ሐ. የሚሊሻ አስተባባሪው ስራውን ለመቀጠል በጤና ረገድ ብቁ መሆኑ በሕክምና ማስረጃ ሲረጋገጥ፣
   መ. የሚሊሻ አስተባባሪው አገልግሎቱን ለመቀጠል ሲስማማ እና፣
   ሠ. የአገልግሎቱን መራዘም ጽ/ቤቱ ሲፈቅድ ይሆናል::

2. Such a duration of service of a militia coordinator may, pursuant to sub-Art.1 of this article hereof, be extended where;
   a. His qualification, special skills, abilities and experience are found to be essential for the duties of the office;
   b. It is certain that it might be impossible to easily find an employee of his replacement;
   c. it is medically proven that the militia coordinator is fit in respect to health so as to carry on his duties;
   d. he consents to the extension of service; and
   e. The office authorizes such an extension.

ክፍል ስድስት
በዲሲፕሊን ኃላፊነት ስለመጠየቅ

PART SIX
LIABILITY WITH REGARD TO DICIPLINARY RESPONSIBILITIES

30. የዲሲፕሊን ቅጣት ዓላማ

የዲሲፕሊን ቅጣት አላማ የሚሊሻ አስተባባሪው በፈፀመው የዲሲፕሊን ጉድለት ተፀፅቶ እንዲታረምና ለወደፊቱ ሥራውን በአግባቡ እንዲያከናውን ማስቻል ሲሆን የማይታረም ሆኖ ሲገኝ ደግሞ ከስራ ማሰናበት ነው::

30. Objective of Disciplinary Penalty

The objective of disciplinary penalties is to rehabilitate the militia coordinator who is found to have committed disciplinary breaches and thus depicts repentance by making him learn from his misdeed and thereby enable him properly perform his duties or to remove him from service if he becomes recalcitrant thereof;

31. ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋቶች

የሚከተሉት በዚህ ደንብ መሠረት ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋቶች ሆነው ተመድበዋል፡-
1. ያለ ፈቃድ ከሥራ መቅረት፤
2. በሥራ ቦታ ተገኝቶ በሥራ ላይ አለመሰማራት፤
3. የሥነ-ሥርዓት ጉድለቶችን ለሚመለከተው ክፍል በወቅቱ አለማሣወቅ፤

31. Simple Disciplinary Offences

The following are, pursuant to this regulation, categorized as simple disciplinary offences:
1. Absence from duty without permission;
2. Failure to be on duty, regardless of appearance at work place;
3. Failure to notify on time disciplinary breaches to the pertinent division;

4. የግል ንጽህናን አለመጠበቅ፤
5. የጦር መሣሪያ ዕዳትን በመጠበቅ ለተግባር ዝግጁ ሆኖ አለመገኘት፤
6. በዚህ አንቀጽ ከተዘረዘሩት ጋር ተመሣሣይነት ያላቸውን ሌሎች የስነ-ስርአት ጉድለቶች ፈፅሞ መገኘት::

4. Failure to care for one's personal hygiene;
5. Failure to get ready for possible actions of practical necessity with keeping firearms clean;
6. Being found to have committed other disciplinary breaches similar to those specified under this article hereof.

32. ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋቶች

የሚከተሉት በዚህ ደንብ መሠረት ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋቶች ሆነው ተመድበዋል:-

1. በህገ-መንግስቱ የሰፈሩትን መሠረታዊና ሰብአዊ ዴሞክራሲያዊ መብቶች ጥሰ መገኘት፤
2. ትዕዛዝ ባለማክበር፣ በቸልተኝነት፤ በመለገም ወይም የአሠራር ሥርአቶችን ባለመከተል በሥራ ላይ በደል ማድረስ፤
3. ከግዳጅ ቦታ መሸሽ፤
4. ሥራ እንዳይሠራ ሆነ ብሎ ማወክ ወይም ከሚያውኩ ጋር መተባበር፤
5. ከማናቸውም ፍርድ ቤት ወይም ስልጣን ያለው ሌላ የፍትህ አካል የሚሰጥን ትዕዛዝ አለማክበር፤
6. በሥራ ቦታ በጠብ አጫሪነት መደባደብ፤
7. በመጠጥ ወይም በአደንዛዥ ዕፅ ሱስ በመመረዝ ሥራን መበደል፤
8. ጉቦ መቀበል ወይም እንዲሰጠው መጠየቅ፤
9. በሥራ ቦታ ለሞራል ተቃራኒ የሆነ ማናቸውንም ድርጊት መፈፀም፤
10. ሥርቆት ወይም የዕምነት ማጉደል ድርጊት መፈፀም፤
11. በጽ/ቤቱ ንብረት ላይ ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት ጉዳት ማድረስ፤
12. በሥልጣን አላግባብ መጠቀም፤
13. ሚስጢር አለመጠበቅ፤

32. Rigorous Disciplinary Offences

The following are, pursuant to this regulation, categorized as rigorous disciplinary offences:

1. violation of the fundamental human and democratic rights stipulated under the constitution;
2. doing harm to an offical duty by being disobedient, negligent, tardy or by non-observance of working procedures;
3. fleeing away from a site of duty;
4. deliberately disturbing or so collaborating with others against carring out of duties;
5. failure to observe orders issued by any court or other competent judicial bodies;
6. engaging in physical violence at work place;
7. causing harm to official duties by being alcoholic or drug addict;
8. receiving bribe or so demanding for same;
9. committing any immoral act at the work place;
10. committing an act of theft or breach of trust;
11. inflicting damage to the property of the office intentionally or by negligence;
12. abuse of power;
13. breach of secrecy;

14. ለሥራ የተረከቡትን የጦር መሣሪያ ማዋስ፣ ማከራየት ወይም ላልተፈቀደለት ሰው ማስታጠቅ፤

15. በቀላል የዲሲፕሊን ቅጣት እርምጃዎች ካለመታረም የተነሣ ከዚህ በላይ በአንቀጽ 31 ስር የተመለከቱትን ጥፋቶች በተደጋጋሚ መፈፀም፤

16. በዚህ አንቀጽ ከተዘረዘሩት ጋር ተመሣሣይ ክብደት ያላቸውን የዲሲፕሊን ጉድለቶች ፈፅሞ መገኘት::

14. lending or renting firearms in his possession in relation to his duties or arming a person unauthorized for the purpose;

15. failure to learn from simple disciplinary measures taken on him and thereby repeatedly commiting offences stated under art. 31 hereinabove;

16. being found to have committed disciplinary breaches of similar gravity as are specified under this article.

33. የዲሲፕሊን ቅጣት አይነቶች

በዚህ ደንብ መሠረት የዲሲፕሊን ጥፋት የፈፀመ ማንኛውም የሚሊሻ አስተባባሪ እንደ ጥፋቱ ክብደት ከሚከተሉት ቅጣቶች አንዱ ሊወሰንበት ይችላል:-

ሀ. የቃል ማስጠንቀቂያ፣

ለ. የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ፣

ሐ. ከወር ደመወዙ ላይ እስከ 10% የሚደርስ መቀጫ፣

መ. እስከ 3 ወር ደመወዝ የሚደርስ መቀጫ፣

ሠ. ከሥራ ደረጃ እና ደመወዝ ዝቅ መደረግ፣

ረ. ለዘለቄታው ከስራ መሰናበት::

33. Types of Disciplinary Penalties

Depending on the gravity of the offence, any one of the following penalties may be imposed on any militia coordinator where he is found to have been committing disciplinary offences pursuant to this regulation:

a. verbal warning;

b. written warning;

c. fine up to 10% of his monthly salary;

d. fine up to three month's salary;

e. demotion from a position of work and its corresponding salary;

f. removal from work indefinitely.

34. የዲሲፕሊን እርምጃ አወሣሰድ

1. በማንኛውም የሚሊሻ አስተባባሪ ላይ የዲሲፕሊን እርምጃ ከመወሰዱ በፊት ፈፀመ የተባለውን የዲሲፕሊን ጉድለት በፅሁፍ እንዲያውቀው ተደርጐ ራሱን የመከላከል ዕድል ይሰጠዋል::

2. በዚህ ደንብ መሠረት ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋቶችን መርምሮ የሚወስነው በየደረጃው የተቋቋመው የዲሲፕሊን ኮሚቴ ይሆናል::

34. Taking of Disciplinary Measures

1. Prior to having taken a disciplinary measure against any militia coordinator, he shall be informed in writing of the alleged breach of discipline and thereby given a chance to defend himself.

2. Simple disciplinary offences shall, pursuant to this regulation, be inquired into and decided upon by the disciplinary

3. ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋቶችን መርምሮ ለበላይ ኃላፊው የውሣኔ ሃሣብ የሚያቀርበው በወረዳ ደረጃ የወረዳ የዲሲፕሊን ኮሚቴ ሲሆን በክልል ደረጃ ደግሞ በጽ/ቤቱ የተቋቋመው የዲሲፕሊን ኮሚቴ ይሆናል::

4. የዲሲፕሊን ቅጣት የማናቸውንም ፍ/ቤት ውሣኔ ሣይጠብቅ ወይም ሣይከተል ሊወሰን ይችላል::

5. ማንኛውም የሚሊሻ አስተባባሪ በከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ምክንያት የተከሰሰና ድርጊቱ ከስራ የሚያስወጣው መሆኑ የተገመተ እንደሆነ ጽ/ቤቱ ከስራ ታግዶ እንዲቆይ ሊያደርገው ይችላል:: ዝርዝሩ ወደፊት በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል::

35. የይግባኝ መብት

1. በቀላል የዲሲፕሊን ጥፋት ምክንያት ቅጣት የተወሰነበት ማንኛውም የሚሊሻ አስተባባሪ በውሣኔው ቅር ከተሰኘ ውሣኔውን የሰጠው የዲሲፕሊን ኮሚቴ ለተቋቋመበት ጽ/ቤት ኃላፊ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል::

2. በከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ምክንያት ቅጣት የተወሰነበት ማንኛውም የሚሊሻ አስተባባሪ የሚኖረውን ይግባኝ አቀራረብ በተመለከተ ዝርዝሩ ወደፊት በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል::

36. ስለይርጋ

1. ቀላል የዲሲፕሊን ቅጣትን የሚያስከትል ጥፋት የፈፀመ የሚሊሻ አስተባባሪ የምርመራ ጊዜውን ሣይጨምር የፈፀመው ጥፋት ከታወቀበት ጊዜ አንስቶ እስከ ሶስት ወር ድረስ እርምጃ ካልተወሰደበት በዲሲፕሊን ተጠያቂ

committee established at various levels.

3. Rigorous disciplinary offences shall be inquired into and recommendations submitted to the managing head either by the woreda or regional disciplinary committees established in their respective jurisdictions.

4. Disciplinary penalties may be imposed irrespective of decisions pending at any court.

5. Where any militia coordinator is accused of committing rigorous disciplinary offences and where such an action is assumed to be entailing his dismissal from job, the office may suspend him for a peride. Details shall be determined by a directive to be issued in the future.

35. Right of Appeal

1. An appeal by any militia coordinator dissatisfied with the decision hereof may be lodged against the verdict of the disciplinary committee with regard to simple disciplinary offences on to the head of the office, wherein such a committee has been established.

2. Any militia coordinator dissatisfied with the penalty imposed on him as regards rigorous disciplinary offences may lodge an appeal in accordance with the specific directive to be issued in the future.

36. Period of Limitation

1. No disciplinary measure shall be put into effect against a militia coordinator who has committed an offence entailing simple disciplinary penalty, unless such measure is taken within three months from the time

አይሆንም::

2. ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣትን የሚያስከትል ጥፋት የፈፀመ የሚሊሻ አስተባባሪ የፈፀመው ጥፋት ከታወቀበት ጊዜ አንስቶ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ በጥፋቱ ካልተከሰሰ በዲሲፕሊን ተጠያቂ አይሆንም::

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ወይም 2 ድንጋጌ ስር በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ መወሰድ የሚገባውን የዲሲፕሊን እርምጃ ሣይወስድ የቀረ ማንኛውም ኃላፊ በህግ ተጠያቂ ይሆናል::

ክፍል ሰባት
በወንጀል ስለተከሰሰ የሚሊሻ አስተባባሪ

37. ከሥራው ጋር በተገናኘ ሁኔታ በወንጀል ስለተከሰሰ የሚሊሻ አስተባባሪ

ማንኛውም የሚሊሻ አስተባባሪ የተከሰሰበትን የወንጀል ድርጊት የፈፀመው በሕግ የተሰጠውን ሥልጣን ሲተገብር በነበረባቸው ሁኔታዎች አስገዳጅነት መሆኑን ጽ/ቤቱ ሲያረጋግጥ ጉዳዩ በዲሲፕሊን ግድፈት የሚያስከትለው ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ:-

1. በሚመለከተው ፍርድ ቤት የዋስ መብቱ ተከብሮለት ከሆነ በሥራው ላይ ሆኖ ሙሉ ደመወዙ እየተከፈለው ይቆያል፤
2. የዋስ መብቱ ሣይከበርለት ቀርቶ በእስር ላይ የሚቆይ ከሆነ:-
   ሀ. ጉዳዩ በፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሣኔ እስኪያገኝ ድረስ ከስራ ይታገዳል፣ ደመወዙም ይያዛል፤

such disciplinary breach was known, excluding the period required for the investigation thereof.

2. No disciplinary measure shall be put into effect against a militia coordinator who has committed an offence entailing rigorous disciplinary penalty, unless such measure is taken within a year from the time the commission of such an offence was known.
3. Any official who has failed to take the disciplinary measures within the time prescribed under the provisions of sub Art 1. or 2 of this article hereof shall be held liable by law.

PART SEVEN
MILITIA COORDINATOR ACCUSED OF CRIME

37. Militia Coordinator Accused of Crime In Relation to his Duties

Where the office has ascertained that any militia coordinator has committed the offence, of which he is accused, while discharging his lawful duties under the coercion of compelling circumstances, without prejudice to the breach entailing disciplinary penalties:

1. He shall be allowed to stay on his duty and thereby receive his full salary provided that he is granted bail by the court concerned;
2. Where he is denied the right to bail and thereby stays in detention: -
   a. He shall be suspended from work and his salary withheld until such time that the court delivers its final desision on the case;

ለ. በተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት ጉዳዩን የያዘው ፍ/ቤት ጥፋተኝነቱን አረጋግጦ የእስራት ወይም የፅኑ እስራት ቅጣት የወሰነበት እንደሆነ ውሣኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከሥራ ይሰናበታል፤

ሐ. የተላለፈበት የእስራት ቅጣት ውሣኔ ከሶስት ዓመት በታች የሆነ እንደሆነና ታሣሪው ከተፈታ በኋላ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ወደ ሥራ ልመለስ ብሎ ከጠየቀ በጽ/ቤቱ ፈቃድ ወደ ሥራው ሊመለስ ይችላል::

3. ክሱ ከቀረበበት ጊዜ አንስቶ የመጨረሻ ውሣኔ እስኪሰጥበት ድረስ የጽ/ቤቱ ነገረ-ፈጅ ስለ ሚሊሻ አስተባባሪው ሆኖ እንዲከራከርለት ሊደረግ ይችላል::

b. he shall be automatically dismissed from his official duties where the court handling the case has found him guilty and passed a sentence of either simple or rigorous imprisonment on him;

c. where the sentence passed against him is to carry less than 3 years of imprisonment, the office may allow him to resume his duties upon his request within one month following his release.

3. The militia coordinator may be represented by the lawyer belonging to the office starting from the time the action was instituted and its final decision was deliverd.

38. ከሥራው ጋር ባልተገናኘ ሁኔታ በወንጀል ስለተከሰሰ የሚሊሻ አስተባባሪ

ማንኛውም የሚሊሻ አስተባባሪ በግልፅ ከታወቀው የሚሊሻ ተግባር ጋር ግንኙነት በሌለው ጉዳይ ክስ ቀርቦበት ከሆነ በዲሲፕሊን ኮሚቴ የሚሰጠው ውሣኔ እንደተጠበቀ ሆኖ:-

1. በሚመለከተው ፍርድ ቤት በዋስ ከተለቀቀ በሥራው ላይ ሆኖ ሙሉ ደመወዙን ያገኛል፤

2. የዋስ መብቱ ሣይከበርለት ቀርቶ በእስር እንዲቆይ ከተደረገ ከስራ ይታገዳል፣ ደመወዙም ይያዛል፤

3. በተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት ጥፋተኛ መሆኑ ከተረጋገጠ ከስራው ይሰናበታል::

38. Militia Coordinator Accused of Crime , not related to his Duties

Any militia coordinator, against whom an accusation has formally been instituted, for an act not releted to an officially – recoganized militia function shall, without prejudice to a decision rendered by the disciplinary committee:

1. get to his job and keep on earning his full salary upon release on bail by the court concerned;
2. be suspended from his duty and his salary withheld provided that he is denied bail and remains in custody;
3. be dismissed from his job once it has been proven that he is guilty of committing the crime he is accused of.

ክፍል ስምንት
ስለልዩ ልዩ ኮሚቴዎች

39. ስለዲሲፕሊን ኮሚቴ

ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣቶችን የሚያስከትሉ ጥፋቶችን የመመርመርና ለጽ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የውሣኔ ሃሣብ የማቅረብ ሥልጣን የተሰጠው የዲሲፕሊን ኮሚቴ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል። ዝርዝር ኃላፊነቱና ስራውን የሚያከናውንበት ሁኔታ በመመሪያ ይወሰናል።

40. ስለደረጃ ዕድገት ኮሚቴ

የሚሊሻ አስተባባሪዎች የደረጃ ዕድገት ጥያቄዎችን መርምሮ ለጽ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ የውሣኔ ሃሣብ የሚያቀርብ የደረጃ ዕድገት ኮሚቴ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል። ዝርዝር ኃላፊነቱና ስራውን የሚያከናውንበት ሁኔታ በመመሪያ ይወሰናል።

PART EIGHT
VARIOUS COMMITTEES

39. The Disciplinary Committee

A disciplinary committee, vested with the powers to investigate and submit recommendations to the managing head of the office with regard to offences entailing rigorous disciplinary penalties, is hereby established, as per this regulation. Its specific responsibilities together with the conditions of its operational environment shall be determined by a directive.

40. Rank Promotion Committee

A rank promotion committee, vested with the powers to submit recommendations to the managing head of the office upon investigation of applications on matters of rank promotion involving militia coordinators, is hereby established, as per this regulation. Its specific responsibilities together with the conditions of its operational environment shall be determined by a directive.

ክፍል ዘጠኝ
ስለሚሊሻ ዓባላት ምልመላ፣ ሥልጠና፣ ሥምሪት፣ መብቶች፣ ግዴታዎችና የዲሲፕሊን እርምጃዎች

41. ስለሚሊሻ ዓባላት ምልመላ

1. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መመዘኛዎች የሚያሟላና ፍላጎት ያለው ማንኛውም ሰው በሚሊሻ ዓባልነት ሊመለመል ይችላል:-

   ሀ. ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ የሆነ፣
   ለ. ለክልሉና ለፌዴራሉ ሕገ-ጋት መንግስታት ታማኝ የሆነ፣
   ሐ. በግሉ ወይም የክልሉ መንግስት ባስታጠቀው መሣሪያ የፀጥታ ጥበቃ አገልግሎት ለመሥጠት የተሟላ አካላዊ ብቃት ያለው፣
   መ. መልካም ሥነ-ምግባር ያለው፣
   ሠ. ማንበብና መፃፍ የሚችል፣
   ረ. ዕድሜው ከ18 ዓመት ያላነሰ፣
   ሰ. በክልሉ ውስጥ መደበኛ ነዋሪ የሆነና ለራሱም ሆነ ለቤተሰቦቹ ቋሚ የገቢ ምንጭ ወይም መተዳደሪያ ያለው::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለሚሊሻ ዓባልነት የሚደረገው ምልመላ በአካባቢው የሚገኙትን ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ተዋጽኦ ከግምት ውስጥ ያስገባ ይሆናል::

PART NINE
SELECTION, TRAINING, ASSIGNEMENT, RIGHTS, OBLIGATIONS AND DISCIPLINARY MEASURES REGARDING MEMBERS OF THE MILITIA

41. Selection of Militia Members

1. Any person wishing to serve as a militia member may, upon fulfillment of the criteria specified below, be selected as such where he:
   a. is an Ethiopian citizen;
   b. is loyal to the Regional and Federal Constitutions;
   c. is physically fit enough to render service on matters of security using firearms of his own or that is given to him by the Regional Government;
   d. has got a good ethical conduct;
   e. is capable of reading and writing;
   f. is not below the age of 18 years;
   g. principally resides in the Regional state and has a permanent of income or livelihood for himself and his family.
2. Without prejudice to the provisions of sub.Art.1 of this article hereof, the selection to be carried out with regard to the militia membership shall take into account the fair representation of nation-nationalities and peoples residing in the Regional State.

42. ስለሚሊሻ አባላት ስልጠና

1. ማንኛውም የሚሊሻ አባል አገልግሎት ከመጀመሩ በፊት መሠረታዊ የሚሊሻ ስልጠና ይሰጠዋል። በተከታታይም ወቅታዊ የተሃድሶ ስልጠና እንዲያገኝ ይደረጋል።
2. የሥልጠናው አላማ ለሕግ የበላይነት የሚቆምና ለፀጥታ ሥራ ብቃት ያለው ህዝባዊ የሚሊሻ ሀይል መፍጠር ነው፣ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።

43. ድጐማ ወይም ማካካሻ ስለማግኘት

በፀጥታ ስምሪት ወቅት በሚደርስ አደጋ ለተሰዋ ወይም ለመስራት የሚያስችለውን አካሉን በከፊል ወይም በሙሉ ለዘለቄታው ላጣ ማንኛውም የሚሊሻ አባል ወይም ቤተሰቡ በዚህ ደንብ መሠረት ለመቋቋሚያ የሚሆን የጉዳት ካሣ ይከፈላል። የካሣ ክፍያ አፈፃፀሙ በየጊዜው ከቢሮው በሚቀርብ መነሻ በክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ውሣኔ የሚሰጥበት ይሆናል።

44. ስለሚሊሻ አባላት ሌሎች መብቶች

ከዚህ በላይ በአንቀጽ 43 ስር የተደነገገው እንደጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የሚሊሻ አባል የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-

1. ከፀጥታ ተግባሩ ጋር በተያያዘ በራሱ፣ በቤተሰቡ ወይም በንብረቱ ላይ ጉዳት ሲደርስ እንደ ጉዳቱ መጠን ከክልሉ መንግስት ቋሚ ወይም ጊዜያዊ የማካካሻ ድጋፍ የማግኘት፤

42. Training of Militia Members

1. Any militia member shall be provided with the basic militia training before commencing his duties. He shall also be given continuous rehabilitative training.
2. With details to be determined by a directive, the objective of the training is to create a peoples' militia force that stands for the rule of law and is efficient enough to under take security works.

43. Gaining Support or Compensatory pay

Any militia member who has been sacrificed due to an accident caused to him during deployment for security duties or who has permanently been deprived of his limbs necessary for his partial or full working capacity or his family shall, pursuant to this regulation, be entitled to a compensatory pay for injuries sustained. The realization of such a compensatory pay shall be determined as per the decision of the council of the Regional Government taking into account the proposal submitted to it from the bureau.

44. Other Rights of the Militia Members

Without prejudice to the provisions of Art .43 hereinabove, any militia member shall have the following rights:

1. to obtain from the Regional Government permanent or temporary payment of compensation where an injury or damage has occurred to his person, family or property, depending on the level of the harm sustained;

2. በሥምሪት ወቅት በአባሉ ላይ የመቁሰል አደጋ ቢከሰት ከመንግስት የሕክምና ተቋማት ነፃ የሕክምና አገልግሎት የማግኘት፣

3. ለፀጥታ ሥራ ከቀበሌው ውጪ ሲንቀሣቀስ የዕለት ቀለብ /ሬሽን/፣ መድሃኒትና ለፀጥታ ሥራ የሚያስፈልጉ ሌሎች ቁሣቁሶችን ከክልሉ መንግስት የማግኘት፣

4. በሚሊሻ ሀይል አባልነት በሚቆይበት ጊዜ ሁሉ የመሣሪያ መጠቀሚያ ግብር ያለመክፈል፣

5. ከፀጥታ ሥራ ጋር በተያያዘ ሶስተኛ ወገኖች በሚያነሱበት ክስ ከጽ/ቤቱ የሕግ አገልግሎት ድጋፍ የማግኘት::

2. to be provided with free medical services from the government health institutions in case of personal injuries recived while in active duties;

3. to obtain ration, medicine and other essentials necessary for the security duties from the Regional Government where he is required to render service outside his place of abode;

4. not to pay tax for the use of firearms during the period of his membership in the militia force;

5. to be provided with legal support services by the office in case of prosecution by third parties with regard to his security duties.

45. ሽልማትና ማበረታቻ ስለማግኘት

በፀጥታ ስምሪት ወቅት ጀብዱ መፈፀማቸው ለተመሠከረላቸው የሚሊሻ አባላት እንደሁኔታው የምስክር ወረቀት ከማግኘት ጀምሮ በገንዘብና በአይነት የተለያዩ ሽልማቶች ሊሰጣቸው ይችላሉ:: ዝርዝሩ ወደፊት በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል::

45. Reward and Incentives

Members of the militia identified to have performed heroic deeds during assignment to security duties may, depending on the circumstances, be granted various awards in cash or in kind starting from gaining a certificate of service. Details shall be determined by a directive to be issued in the future.

46. የሚሊሻ አባላትን ስለማሰናበት

1. በሚሊሻ አባልነት ለረዥም ጊዜ አገልግሎት የሰጡና በዕድሜ ምክንያት በስራቸው ለመቀጠል የማይችሉ አባላት በክብር እንዲሰናበቱ ይደረጋል::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የሰፈረው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የሚሊሻ አባል በሥራው ለመቀጠል ያልፈለገ እንደሆነ በማናቸውም ጊዜ ስንብት ጠይቆ የመውጣት መብቱ የተከበረ ነው:: ዝርዝር አፈፃፀሙ

46. Releasing Militia Members

1. Militia members who have served long overdue and are thereby unable to carry on rendering service due to old age shall be released in honor.

2. Without prejudice to the provision of sub art (1) of this article hereof, any militia member wishing not to carry on his duties shall have the write to resign any time upon request. Details of the implementation shall

ወደፊት በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል::

47. ስለሚሊሻ አባላት ግዴታዎች

ማንኛውም የሚሊሻ አባል ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ግዴታዎች ይኖሩበታል:-

ሀ. ቀላልም ሆነ ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋቶችን ከመፈፀም የመቆጠብ፤

ለ. አደጋ የደረሰበት አባል አፋጣኝ እርዳታ እንዲያገኝ አስፈላጊውን ድጋፍ የመስጠት፤

ሐ. ትጥቅን በአግባቡ የመያዝና የጥይት ብክነትን የመከላከል፤

መ. ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ካላጋጠመ በስተቀር የፀጥታ ሥራን ያለበላይ አመራር ፈቃድ ያለማቋረጥ፤

ሠ. ከመንግስት የተሰጠን ትጥቅ ለሌላ ሰው አሳልፎ ያለመስጠት፤

ረ. ከወንጀለኞችና ፀጥታን ከሚያደፈርሱ ህገ-ወጥ ሀይሎች ጋር ያለመተባበር::

48. የዲሲፕሊን ተጠያቂነት

ለዚህ ክፍል ድንጋጌዎች አፈፃፀም የዲሲፕሊን ቅጣት ዓላማ የህዝብ አገልጋይና ቅን የሚሊሻ አባላት እንዲኖሩ ማስቻል ሲሆን ከጥፋታቸው ለመታረም ዝግጁ ያልሆኑትን ደግሞ ከአባልነት ማስወገድ ይሆናል::

49. ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋቶች

ከዚህ በታች የተመለከቱት የሚሊሻ አባላትን በዚህ ደንብ መሠረት የሚያስጠይቁ ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋቶች ሆነው ተመድበዋል:-

1. ያለበቂና ህጋዊ ምክንያት በስምሪት ቦታ አለመገኘት፤

2. የተሰጠ ተግባርን በተነሣሽነት አለመፈፀም፤

3. ከሌሎች አባላት ጋር ተግባብቶ አለመስራት፤

be determined by a directive to be issued in the future.

47. Obligations of the Militia Members

Any militia member shall have the following spasific obligations:

a. to refrain from committing simple or rigorous disciplinary offences;

b. to provide necessary support for an injured member so that the latter may have access to an immediate assistance thereof.

c. to properly handle firearms and thereby prevent wastage of bullets;

d. not to sever security duties without the permission of the top management, save reasons encountered due to force majeure.

e. not to transfer firearms supplied to him by the government on to any other person;

f. not to collaborate with those criminals and unlawful elements destabilizing security.

48. Disciplinary Liability

The main objective of disciplinary penalties shall, for the implementation of the provisions of this part, to make it possible for the existence of militia members who are faithful and committed to serving the community and hence to do away with those unprepared to correct and rectify their misdeeds.

49. Simple Disciplinary Offences

The following are hereby categorized as simple disciplinary offences whereby members of the militia might be liable, as per this regulation:

1. absence from a place of assignment without sufficient and lawful cause;

2. failure to carryout duties on one's assignement out of initiation;

3. failure to work in harmony with other

4. ለመሣሪያ ደህንነት ተገቢውን ጥንቃቄ አለማድረግ፤
5. ምስጢር አለመጠበቅ::

50. ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋቶች

ከዚህ በታች የተመለከቱት የሚሊሻ አባላትን በዚህ ደንብ መሠረት የሚያስጠይቁ ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋቶች ሆነው ተመድበዋል:-

1. መሣሪያ ማዋስ፣ ማከራየት ወይም ባልባሌ ቦታ ማስቀመጥ፤
2. በሌላ አባል ላይ መሣሪያ ማዞር ወይም ጠብ መጫር፤
3. ተገቢ ባልሆነ ጊዜ ወይም ባልተፈቀደበት ስፍራ መተኮስ፤
4. ከህገ-ወጥ ሀይሎች ጋር መደራደር፤
5. ከግዳጅ መሸሽ፤
6. ጓደኛን ለአደጋ ማጋለጥ፤
7. አዘውትሮ በመስከር ለስምሪት ብቁ ሆኖ አለመገኘት፤
8. ስርቆት መፈፀም ወይም በሃሰት መመስከር፤
9. ከቸልተኝነት፣ ከልማመኝነት ወይም ትዕዛዝ ካለማክበር የተነሣ በተልዕኮ ላይ በደል ማድረስ፤
10. ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ጋር ተመሣሣይ የሆነ ጠባይ ያላቸውን አድራጐቶች መፈፀም፤
11. ቀላል የዲስፕሊን ጥፋቶችን ለተደጋገመ ጊዜ ፈፅሞ መገኘት::

members;

4. failure to take proper care in respect to the safety of firearms;
5. breach of secrecy.

50. Rigorous Disciplinary Offences

The following are hereby categorized as rigorous disciplinary offences whereby members of the militia might be liable, as per this regulation:

1. lending, renting or keeping firearms in an unsafe way;
2. turning fire against another fellow member or provocation of violence;
3. shooting in an improper time or at a place where such an act is not officially permitted;
4. Bargaining with unlawful forces;
5. running away from one's duties;
6. endangering a work-mate;
7. incompetence for possible assignment due to regular intoxication;
8. committing theft or perjury;
9. doing harm to a mission as a result of one's negligence, insensitivity or disobedience;
10. committing acts of similar nature as those spesified hereinabove,
11. being found to have repeatedly committed simple disciplinary offences.

51. በዲሲፕሊን ጥፋት ምክንያት ስለሚወሰዱ እርምጃዎች

1. በዚህ ደንብ መሠረት የዲሲፕሊን ጥፋት የፈፀመ ማንኛውም የሚሊሻ አባል እንደጥፋቱ ክብደት ከሚከተሉት ቅጣቶች አንዱ ሊወሰንበት ይችላል፦

   ሀ. የቃል ማስጠንቀቂያ ወይም ተግሣፅ፤
   ለ. የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ፤
   ሐ. እስከ አንድ ወር ለሚደርስ ጊዜ ትጥቅ ማስወረድ፤
   መ. ከሶስት እስከ ስድስት ወር ለሚዘልቅ ጊዜ ትጥቅ ማስወረድ፤
   ሠ. ላልተወሰነ ጊዜ ትጥቅ ማስወረድ፤

   ረ. ከአባልነት ማሰናበት::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር ከፊደል ተራ ቁጥሮች ሀ እስከ ሐ የተዘረዘሩት በቀላል የዲሲፕሊን ጥፋት ምክንያት የሚወሰዱ እርምጃዎች ሲሆኑ ከፊደል ተራ ቁጥሮች መ እስከ ረ የተመለከቱት ደግሞ በከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ሣቢያ የሚወሰኑ ቅጣቶች ናቸው::

52. ስለ ውሣኔ ሰጪ አካላት

1. ቀላል የዲሲፕሊን እርምጃዎች የሚወሰዱት በቀበሌ የሚሊሻ አመራር ሲሆን ከባድ የዲሲፕሊን ጉዳዮች ግን በወረዳ የሚሊሻ አመራር ተጣርተው የሚወሰኑ ይሆናል::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተጠቀሱት አካላት ዝርዝር ኃላፊነትና ስራቸውን የሚያከናውኑበት ሁኔታ ወደፊት በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል::

51. Measures to be taken due to Disciplinary Offences

1. Depending on the gravity of the offence, any one of the following penalties may be imposed on a militia member who commits disciplinary offences pursuant to this regulation:
   a. verbal warning or rebuke;
   b. written warning;
   c. disarmament for a period up to one month;
   d. disarmament for a period lasting from three to six months;
   e. disarmament for an unlimited period of time;
   f. dismissal from membership.
2. The penalties specified under sub art.1 a-c of this article hereof are measures to be taken due to simple disciplinary offences, whereas those specified under d -f of same are measures to be taken due to rigorous disciplinary offences.

52. Decision-Making Bodies

1. simple disciplinary measures shall be taken by the leadership of the kebele militia, where as rigorous disciplinary cases may be inquired into and decided upon by the woreda militia leadership.
2. Detailed responsibilities and working conditions of the bodies specified under sub art (1) of this article hereof shall be determined by a directive to be issued in the future.

ክፍል አሥር
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

53. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጐች

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሌላ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ ደንብ ውስጥ በተሸፈኑት ጉዳዩች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም::

54. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ቢሮው ይህንን ደንብ በተሟላ ሁኔታ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል::

55. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ መንግስት ዝክረ-ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

ባህር ዳር
ሚያዚያ 3 ቀን 1997 ዓ.ም
ዮሴፍ ረታ
የአማራ ብሔራዊ ክልል
ርዕሰ መስተዳድር

PART TEN
MISCELLANEOUS PROVISIONS

53. Inapplicable Laws

Any other regulation, directive or customary practice inconsistent with this regulation may not apply to matters provided for in this regulation.

54. Power to Issue Directives

The Bureau may issue directives necessary for the full implementation of this regulation.

55. Effective Date

This regulation shall come into force as of the date of its publication in the Zikre Hig Gazette of the Regional State.

Done at Bahir Dar
This 11th day of April, 2005
Yosef Reta
Head of Government of the Amhara
National Regional State